# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፦** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

**ሚያዚያ 06 ቀን 2005 ዓ.ም**

**በፌዴራል ፖሊስ እየተደበደቡ የተባረሩ የአማራ ብሔር ተወላጆች ወደ ቦታቸው ይመለሱ መባሉ ማስመሰያና ማታለያ ነው ተባለ፤**

**የወያኔ ካድሬዎች ጥያቄ ማንሳታቸው ታወቀ፤**

**የእነ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ጉዳይ አሁንም እያወዛገበ መሆኑ ተገለጸ፤**

**ጋዜጠኛ ርዕዮት አለሙ በከፋ የጤና መታወክ ላይ ትገኛለች ተባለ፤**

ባለፉት ሁለት ሳምንታት ከ30 ሺህ በላይ የሆኑ የአማራ ብሔር ተወላጆች ከቤንሻንጉል ክልል ከተለያዩ ወረዳዎች ይኖሩበት ከነበረው ቀዬ አፈናቅሎ ወደ ጎጃም ፍኖተ ሰላም እንዲሰደዱ ያደረገው የወያኔ ቡድን ሰሞኑን መልሶ ወደነበሩበት ስፍራ እንዲመለሱ ሲል የማስመሰያ ጥሪ ማቅረቡ ታውቆዋል።

ከ20 ዓመታት በላይ ይኖሩበት ከነበረው ቦታ ላይ እንዲፈናቀሉ ትዕዛዝ የሰጡት የወያኔ ቱባ ባለስልጣናት በደረሰባቸው የዓለም አቀፍ ጫናና የህዝብ ተቃውሞ ምክንያት እንደ እቃ ጭነው ያባረሩዋቸውን ዜጎች ወደ ነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ ጥሪ ከማቅረባቸውም በላይ ድርጊቱን የፈጸሙት የበታች ሹማምንቶች እና የወረዳ ባለስልጣናት በመሆናቸው ሊጠየቁ ይገባል ሲሉም በራሳቸው ካድሬዎች ላይ ጣታቸውን መቀሰራቸው ታውቆዋል።

በባህር ዳር ከተማ 9ኛ ጉባኤውን አድርጎ በኩርፊያና በሽኩቻ የተበተነው የወያኔ ቡድን የአዲስ አበባን ሕዝብ በምርጫው ለማሳተፍ እና ከጎኑ ለማድረግ በማሰብ በየክፍለ ከተማው ቱባ ቱባ ባለስልጣናቱን ልኮ ከህዝቡ ጋር ለመነጋገር ሙከራ ያደረገ ቢሆንም በሁሉም ክፍለ ከተማ የተገኘው ሕዝብ እኛ ማነን...ሀገራችንስ የት ነው...የኤርትራ ዜጎች በስደት መጥተው ስራ ሲሰጣቸው የአማራ ብሔር በችግር ምክንያት ከዓመታት በፊት በቤንሻንጉል ክልል በመስፈሩ እንደ ባዕድ ከመባረሩ ባሻገር ያፈራውን ሀብትና ንብረት ሳይዝ ባዶ እጁን እንዲሰደድ መደረጉ ወንጀል ከመሆኑም ባሻገር ይኼን

እርምጃ የወሰደው አካል በይፋ በህግ ሊጠየቅ ይገባል ......ይሄ ሲሆን ብቻ ነው ውይይቱን ልንቀጥል የምንችለው በማለት አቋዋም በመያዛቸው ባለስልጣናቱ በመደናገጥ ለተሰብሳቢዎቹ የተፈናቀሉ ዜጎች በአስቸኳዋይ ይመለሳሉ በማለት ቃል በገቡ በሁለት ቀናት ውስጥ የተሰደዱ ዜጎች ወደነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ ጥሪ መደረጉ ታውቆዋል::

ቦታው ለከተማ ምስረታ.....ለህንጻዎች እና ለቢሮዎች መስሪያ እንደሚፈለግ አስቀድሞ የተነገራቸው መሆኑንና እንዲፈናቀሉ ትዕዛዝ መስጠቱን በልበ ድፍንነት ከሁለት ሳምንት በፊት በይፋ በሚዲያ የገለጸው የክልሉ ፕሬዝዳንት አህመድ ናስር የተባለው የወያኔ ተላላኪ ሰኞ መጋቢት 30 ቀን 2005 ዓ.ም ደግሞ እንደገና ዜጎቹ የተፈናቀሉት በበታች ባለስልጣናት እና በወረዳ ካድሬዎች ስህተት ስለሆነ ዜጎቹ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ሲል ከበላዮቹ የተሰጠውን የማስመሰያ ትዕዛዝ ያስተላለፈ መሆኑና ተፈናቃዮቹም ለሞቱት ወገኖቻችን ተጠያቂው ማነው....የጠፋው ንብረትም ይተካልን......በማለት ጥያቄ ማቅረባቸው ታውቋል::

የወያኔ ባለስልጣናት በየክፍለ ከተማው የቀረበባቸውን ብርቱ ነቀፋና ትችት...የብአዴን የወረዳና የዞን ባለስልጣናት ያነሱት የማንነት ጥያቄ .....የዓለም አቀፍ ተቃውሞን ተከትሎ አጣብቂኝ ውስጥ ስለገቡ ስህተቱን በበታች ባለስልጣናት ላይ በማላከክ ዜጎቹ ይመለሱ እያሉ ከመወትወታቸውም በተጨማሪ የመመለሻ መኪና ማቅረባቸው እጅግ አስገራሚና አሳፋሪ የወያኔ ድርጊት ነው ተብሎዋል::

ከኖሩበት ቀዬ ሲባረሩ ያፈሩትን ሀብትና ንብረት ሳይዙ ባዶ እጃቸውን እንዲወጡ ተደርገው፤ እያንዳንዳቸው 350 ብር እንዲከፍሉ ተገድደው በአንድ ጭነት መኪና 80 ሰው እንደ እቃ ታፍገው ተወስደው ከፊሉም በመኪና አደጋ ህይወቱ አጥቶ ሕይወታቸው የተረፈውም በአልባሌ ቦታ በሰቃይ እንዲቀመጡ ተደርገው ከፍተኛ በደል ከደረሰባቸው በኋላ አሁን የወያኔ መሪዎች ባንዳንደ ጫናዎች ተፈናቃዮቹ ወደ ቤታቸው ይግቡ ብለው አውቶቡስ ማቅረባቸው በበዜጎች ላይ የፈጸሙትን የሚያሳፍር እና የሚያሳዝን አረመኔያዊ ተግባርና ለዜጎች ያላቸውን ንቀት የሚሸፍን አይደለም በቁጭት የሚናገሩ ዜጎች በርከታ ናቸው::

ተፈናቃይ ዜጎቹ እጅግ በሞራልም ሆነ በገንዘብ ክፉኛ ከመጎዳታቸውም በላይ አባት ልጆቹንና ሚስቱን ያጣበት..... ልጆች እናትና አባታቸውን የተነጠቁበት .....ባል እንደወጣ ሳይመለስ የሄደበት......ሚስት በምጥ አድኑኝ እያለች ያሸለበችበት .....የእምነት አባቶች ድርጊቱን አናይም እያሉ ከመኪና እየዘለሉ የሞቱበት ሲሆን ይህን አረመኔ ተግባር የፈጸሙ የወያኔ መሪዎች ሀጢያቱን ትዕዛዝ በሰጡዋቸው የበታች ባለስልጣናት ላይ አላክከው ኪራይ ሰብሳቢ የሆኑ የበታች አመራሮች የፈጠሩት ችግር ነው በማለት ከተጠያቂነት ሊያመልጡ ላይ ታች እያሉ ሲዘሉ መታየታቸው በእጅጉ የሚያሳፍር እና የሚያንገበግብ አሳዛኝ ነው ሲሉ እነዚሁ የመሀል ሀገር ነዋሪዎች እንባ እየተናነቃቸው ይናገራሉ::

ከቤንሻንጉል ክልል ከመተከል ዞን የተፈናቀሉት ዜጎች ጥሪ ሳይደረግላቸው ከማሽ ዞን ያሶ ወረዳ ብቻ የተፈናቀሉትን ዜጎች እንዲመለሱ ማድረጉ ወያኔ የደረሰበትን የፖለቲካ ውጥረት ለማርገቢያ የወሰደው መሆኑን ጉዳዩን የሚከታተሉ ወገኖች ተናግረዋል::

የወያኔ ባለስልጣናት እነዚህን ሰዎች ለመመለስ ግዴታ የሆነባቸው ሕዝቡ ሰፊ የተቃውሞ እንቅስቃሴ በማድረጉና ካድሬዎች ባነሱት ጥያቄ......ውጥረት ውስጥ በመግባታቸው ሲሆን የወሰዱት እርምጃ ለማስታገስ ያህል እንጂ ከልብ አምነውበት እንዳልሆነ ጉዳዩን የሚከታተሉ ወገኖች ይናገራሉ:::

ከዚህ በፊት ከቤንች ማጂ ዞን ከጉራ ፈርዳ ወረዳ የተፈናቀሉ የአማራ ብሔር ተወላጆችን በተመሳሳይ መልኩ ጨንቱና ውጥረቱ ሲበዛ ከብአዴን አንድ ተወካይ ተደርጎ አዲስ አበባ የገቡትን መልሰው ወደ ቦታቸው አድርሰዋቸው ነበር።ነገር ግን ከወሰዱዋቸው ከአንድ ሳምንት በሁዋላ በተናጠል እየከፋፈሉ አባርረዋቸው በአሁኑ ሰዓት የት እንዳሉ እንኩዋን አይታወቅም። የቤንሻንጉል ተፈናቃዮችም እንዲሁ ሊያደርጉዋቸው ይችላሉ በማለት ጉዳዩን በአንክሮ የሚከታተሉ ወገኖች ስጋታቸውን ይገልጻሉ።

በተለይ በጎጃም እና በጎንደር ውስጥ ያሉ የወረዳ ካድሬዎች በአማራ ብሔር ተወላጆች ላይ በደረሰው የመፈናቀል አደጋ ዙሪያ ተወያይተው ድርጊቱን በማውገዝ አንድ አይነት አቋዋም ከመያዛቸውም በተጨማሪ የብአዴን ሊቀመንበር ደመቀ መኮንን እና የቀድሞውን ሊቀመንበር አዲሱ ለገሰን በጉዳዩ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡ ቢጠሩዋቸውም ሳይገኙ መቅረታቸውን ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል።

ካድሬዎቹ በአማራ ላይ እየተወሰደ ያለው አሰቃቂ እርምጃ መቆሚያው የት ነው......የህወሀት ጉዳይ አስፈጻሚስ የምንሆነው እስከ መቼ ነው.....ውክልናችን ለየትኛው ሕዝብ ነው.......ይሄ ጉዳይ በድርጅታችን በኩል መልስ ሊሰጠን ይገባል በሚል ከተለያዩ ወረዳዎች ተሰባስበው እና በስልክ ተገናኝተው ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ደመቀ መኮንን እና አዲሱ ለገሰ የተባሉት የህወሀት ተላላኪዎች ባይቀርቡም የብአዴን ምክትል ሊቀመንበር ደጉ አንዳርጋቸው የተባለው ግለሰብ ችግሩ በአጭር ቀን እንደሚፈታ ቃል ገብቶ መልስ እንደሰጣቸውም ከፍኖተ ሰላም የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል።

በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በመተከል እና በከማሽ ዞን ውስጥ ሲኖሩ በነበሩት የአማራ ብሔር ተወላጆች ላይ የደረሰው ዘግናኝ እና አሰቃቂ የሞራል እና የሰብአዊ ግፍ ምንም ሳይመስላቸው ወደ ነበሩበት ቦታ ይመለሱ ብለው እንደቀላል ነገር ትዕዛዝ የሰጡት የወያኔ ቡድን መሪዎች ለፈጸሙት ጥፋት አንዳችም የመፀፀት ነገር ካለማሳያታቸውም ባሻገር በደረሰባቸው ጫና ምክንያት የሰሩትን ወንጀል ለማድበስበስ 21 አውቶቡሶችን አቅርበው በግድ እንዳባረሩዋቸው በግዳጅ አፍሰው እንደገና ሲጭኑዋቸው በስፍራው ከነበሩ የአይን እማኞች የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል።

በአማራ ብሔር ተወላጆች ላይ የደረሰውን ዘግናኝ በደል ተከትሎ በጎንደር ...በጎጃም... በሰሜን ሸዋ...በወሎ እና በሌሎችም ክልሎች የተነሳውን የካድሬዎች ጥያቄ ለማዳፈን እና ካድሬዎቹን ለመከፋፈል የምርጫ ወቅት በመሆኑ ሁሉም ወደ የገጠር ወርዶ መስራት አለበት በሚል እነ በረከት ስምኦን ደብዳቤ ከኢህአዴግ ጽህፈት ቤት ባወጡት መልእክት የበተኑ ቢሆንም በአማራ ክልል ውስጥ ግን ጥሩ ነገር እየታየ ባለመሆኑ የወያኔን ቁንጮ መሪዎች ያሳሰባቸው መሆኑን ለባለስልጣናቱ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ሲገልጹ ተደምጠዋል።

ጉዳዩ ወደ መከላከያ ውስጥ እንዳይገባ ታፍኖ እንዲቀመጥ ጥረት እየተደረገ የሚገኝ ቢሆንም አሁን ባለው ሁኔታ በተለይ የካድሬዎቹ ጥያቄ በዚሁ ከቀጠለ በወያኔ ቡድን ውስጥ እሳት ሊፈጥር ይችላል ተብሎ ስጋት ማሳደሩንም ለባለስልጣናቱ ቅርበት ካላቸው ወገኖች ይሰማል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በሽብርተኝነት እና በሀገር ክህደት ተወንጅለው ከ8 ዓመት እስከ እድሜ ልክ እስራት የተፈረደባቸው የእነ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ የይግባኝ ጉዳይ በዳኞች እና በዓቃቤ ህጎች መሀከል ውዝግብ በማስነሳቱ ለሌላ ግዜ ቀጠሮ መሰጠቱ ታወቀ።

የከፍተኛ ፍርድ ቤት 4ኛ ወንጀል ችሎት ከ8 ዓመት እስከ እድሜ ልክ እስራት የፈረደባቸው እነዚሁ የሕሊና እስረኞች ይቅርታ ጠይቀው ከእስር ሊለቀቁ እንደሚችሉ ቢነገራቸውም ቀድሞም ያጠፉነው ጥፋት ስለሌለ ወያኔን ይቅርታ አንጠይቅም በማለት የተፈረደባቸው አግባብ እንዳልሆነ በማጣቀስ ይግባኝ ቢጠይቁም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች ዳኜ መላኩ እና አማረ ማሞ ጉዳዩን መርምረው ሊያስቀጣቸው የሚያስችል አንድም ፍሬ ነገር ባለማግኘታቸው በነጻ ሊያሰናብቱ እንደሆነ በቃል በመናገራቸው የተበሳጩት የወያኔ ተላላኪና ጉዳይ አስፈጻሚ የሆኑት ዓቃቤ ህጎች እስከ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተብየው ድረስ በማመልከታቸው በአሁኑ ሰዓት ውሳኔ ሳይሰጥ ለአምስተኛ ግዜ ለሚያዚያ 24 ቀን 2005ቀጠሮ መያዙ ታውቆዋል።

መጀመሪያ ፋይሉ ተሰጥቶት የተመለከተው አማረ ማሞ የተባለው ዳኛ በደንብ አይቶ ጉዳዩን ካጤነ በሁዋላ አቃቤ ህግ የመሰረተው ክስ አግባብ እንዳልሆነ.....የቀረቡባቸው ማስረጃዎች እና ምስክሮች ከተከሰሱበት ጭብጥ ጋር ፍጹም የማይገናኝ ሆኖ በማግኘቱ በነጻ ሊለቃቸው መሆኑን በመናገሩ ፋይሉ ተነጥቆ ለዳኜ መላኩ ቢሰጠውም በተመሳሳይ ይሄኛውም ዳኛ የመጀመሪያውን ሀሳብ በማንጸባረቁ በሕወሀት አባል በሆኑት በዓቃቤ ህጎቹ እና የብአዴን አባል በሆኑት ዳኞች መሀከል ከፍተኛ ውዝግብ ከመፈጠሩም ባሻገር በቃላት ጦርነት ውስጥ መግባታቸውን ተከትሎ በደመቀ መኮንን ሸምጋይነት ለግማሽ ቀን የፈጀ ዝግ ስብሰባ ማድረጋቸውን የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ አስረድተዋል።

በተደረገው በዚሁ ዝግ ስብሰባ የህወሀት አባል የሆኑ ዳኞችም ከአቃቤ ህጎች ጋር በመወገን በሽብርተኝነት የተከሰሱት ወንጀለኞች በመሆናቸው ፍርዱ አንሱዋቸዋል እንጂ አይበዛባቸውም ስለዚህ በዚሁ ሊቀጥል ይገባል ሲሉ የብአዴን አባል የሆኑ ዳኞች ደግሞ አንዳችም ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ ለፖለቲካ ፍጆታ ተብሎ የሀገሪቱን ገጽታ የሚያጠፋ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም በሚል የተከራከሩ ሲሆን በሽምጋይነት የተቀመጠው ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ደመቀ መኮንን ዳኞቹም ሆነ አቃቤ ህጎቹ ያሉትን ሀሳብ ተቀብሎ ሁለቱም ትክክል እንደሆኑ ገልጾ ነገር ግን በአሁኑ ሰዓት የተያያዝነውን የአምስት ዓመት የትራንስፎርሜሽን እቅዱ እንዳይደናቀፍብንና እቅዳችንን ለማሳካት እንድንችል ለዓለም አቀፍ ጫና መሸነፍ አለብን.....በመሆኑም የእስረኞቹ ጉዳይን በሰከነ መንገድ ታይቶ ቢወሰን የተሻለ ይሆናል ብሎ የራሱን ውሳኔ ሳይሰጥ በፍርሀት ስብሰባው እንደተበተነ ከውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል።

በዚህም መሰረት ለአራተኛ ግዜ ሰኞ መጋቢት 30 ቀን 2005 ዓ.ም ተቀጥሮ የነበረውን ጉዳዩ በደንብ መመልከት እና ማጤን የሚያስፈልገው በመሆኑ አሁንም ሌላ ቀጠሮ መስጠት ያስፈልጋል

በማለት ለሚያዚያ 24 ቀን 2005 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቶዋቸው ሊበተን እንደቻለ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

በቅርቡ ከፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር በተላከ አንድ ቡድን በተደረገ ግምገማ ሙሰኛ እና ዘረኛ መሆኑ የተረጋገጠው አብርሀም ወ/አረጋይ የተባለው የቃሊቲ እና የቅሊንጦ እስር ቤቶች የበላይ ጠባቂ ትዕዛዝ ሰጪነት በእስረኞቹ ላይ የተለያዩ ግፎች እየተፈጸሙባቸው መሆኑን ቤተሰቦቻቸው እያለቀሱ ሲናገሩ መደመጡንም የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

በተያያዘ ዜና በሽብርተኝነት ተከስሳ በቃሊቲ እስር ቤት የምትገኘው ጋዜጠኛ ርዕዮት ዓለሙ የተለያዩ ጫናዎች በእስር ቤቱ ኃላፊዎች እየደረሰባት መሆኑን ቤተሰቦችዋ እና የዓለም አቀፉ የጋዜጠኞች መብት ተሙዋጋች በይፋ ገለጹ፡፡

ጋዜጠኛ ርዕዮት ከዚህ በፊት ይቅርታ እንድትጠይቅ ተደጋጋሚ ግዜ በወያኔ ቡድን ግፊት ቢደረግባትም አሳሪው ክፍል ይቅርታ ጠይቆኝ ሊፈታኝ ይገባል እንጂ እኔ ይቅርታ አልጠይቅም ብላ አቁዋም በመያዝዋ በአሁኑ ሰዓት የተለያዩ ጫናዎች እየደረሱባት መሆኑን ከቃሊቲ እስር ቤት የደረሰን ጥቆማ ገልጾዋል፡፡

ከተለያዩ ጫናዎች እና ከንጽህና መጠበቅ ጉድለት እንዲሁም ከምግብ አቅርቦት ጋር በተያያዙ በሚመጡ በሳይነስ..... በጨጉዋራ እና በጡት ህመም እየተሰቃየች መሆንዋን ያጋለጡት ወላጅ አባትዋ በአሁኑ ሰዓት ጥሩ ሁኔታ ላይ እንዳልሆነችም ገልፀዋል፡፡

ባለፈው ክረምት ወር ውስጥ በአንደኛው ጡትዋ ላይ እጢ በቅሎ በቀዶ ህክምና እንዲወጣላት ቢደረግም ተከታታይ ህክምና ማድረግ ሲገባት በእስር ቤቱ ኃላፊዎች በመከልከልዋ መልሶ የተካ በመሆኑ በአሁኑ ሰዓት ለከፋ የጤና መታወክ እንደተዳረገችና አልፎ ተርፎ ወደ ህክምና እንዳትሄድ ተከልክላ እንደምትገኝ ወላጅ አባትዋ ገልጸዋል፡፡

የዲስፒሊን ግድፈት ፈጽመሻል.....የእስር ቤቱን ሰራተኞች እና ኃላፊዎች አታከብሪም..... የምትሰሩትን ስራ በጋዜጣና በሚዲያ እንዲነገር አደርጋለሁ እያልሽ ታስፈራሪያለሽ ......ለባለስልጣናቱ አክብሮት የለሽም .......የታሰርሽበት ምክንያት ለእስረኞቹ አርአያ የሚያደርግሽ አይደለም በማለት የተለያዩ ምክንያቶችን ደርድረው ሌላ አዲስ ክስ በማረሚያ ቤቱ እንደተመሰረተባትም ወላጅ አባትዋ ተናግረዋል፡፡

የእስር ቤቱ ኃላፊ አብርሀም አረጋዊ የተባለው የህወሀቱ ባለስልጣን ሰሞኑን አዲስ ክስ እንዲመሰረትባት አድርጎ ለፖሊስ ቃል እንድትሰጥ የሆነው የአመክሮ ግዜዋን ለመውሰድ ተብሎ እንደሆነ ያጋለጡት የቃሊቲ እስር ቤት ፖሊሶች ይህ ካልሆነ በቀር ከሌሎቹ እስረኞች የተለየ አንዳችም የምታደርገው እንቅስቃሴ እንደሌለ ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡

በቅርቡም የሁለተኛ ዲግሪዋን ለመማር እንዲያስችላት ከእስር ቤቱ ኃላፊዎች ፍቃድ አግኝታ ከ26 ሺህ ብር በላይ ከፍላ በርቀት ትምህርት ሊያስተምራት ከሚችለው ኮሌጅ ጋር ውሉዋን ፈጽማ መጻኅፍቶችን ተረክባ የነበረ ቢሆንም የእስር ቤቱ ኃላፊ የህወሀቱ አብርሀም አረጋዊ ግን የፖለቲካል ሳይንስ የምትማሪ በመሆኑ ከልክለናል ብሎ እንዳገደባትም ከቤተሰቦቿዋ የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

ሲፒጄ የተሰኘው ዓለም አቀፍ የጋዜጠኞች መብት ተከራካሪ ድርጅት በበኩሉ በአሸባሪነት ተከስሳ በቃሊቲ እስር ቤት በምትገኘው ጋዜጠኛ ርዕዮት ዓለሙ ላይ የእስር ቤቱ ኃላፊዎች የተለያዩ ጫናዎች እና ወከባዎች እያደረሱባት ነው ሲል ገልጾዋል፡፡

ቃሊቲ እስር ቤትን ጨምሮ በመላ ሀገሪቱ ያሉ እስር ቤቶች እጅግ አደገኛ የበሽታ ማስፋፊያ በመሆናቸው ቁጥራቸው የበዙ እስረኞች በየግዜው እየሞቱ መሆኑን ከተለያዩ እስር ቤቶች የደረሰን ጥቆማ ገለጸ፡፡

በተለይ በኦሮሚያ ክልል እስር ቤቶች ውስጥ እስረኞች ንጽህናቸውን እንዳይጠብቁ በቂ የውሀ አቅርቦት እንዳያገኙና ሳሙና የማይሰጣቸው በመሆኑ የተባዮች መራቢያ በመስፋፋቱ በተላላፊ በሽታዎች እየተጠቁ እጅግ ቁጥራቸው የበዛ እስረኞች እያለቁ መሆኑን ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

በነቀምት....በደምቢዶሎ.....በአምቦ.....በወሊሶ.....በቦረና ከፖለቲካ ጋር በተያያዘ በጅማ.....በሐረር....በሻሸመኔ...በአዳማ/ናዝሬት....እና በሌሎች እስር ቤቶች ደግሞ ከእምነት ጥያቄ ጋር በተያያዘ በታሰሩ ዜጎች ላይ ይህ ቀረሽ የማይባል አስከፊ በደል እየተፈጸመባቸው ከመሆኑም በጨማሪ እስረኞቹ ንጽህናቸውን ጠብቀው ከበሽታ እራሳቸውን እንዳይከላከሉ በመደረጉ በየቀኑ ከየእስር ቤቶቹ በተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች እየሞቱ አስከሬናቸው ለቤተሰቦቻቸው እንደሚሰጥ ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

እስረኞቹ በሚደርስባቸው የከፋ በደል የተነሳ በየግዜው የዓለም አቀፍ ድርጅቶች መጥተው እንዲያዩዋቸው ጥሪ እያደረጉ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ ሊደርስላቸው የቻለ ድርጅት ባለመኖሩ የተነሳ በርካታ እስረኞች እየሞቱ እንደሚገኝ ከተለይዩ እስር ቤቶች የደረሱን ጥቆማዎች አጋልጠዋል፡፡

በቃሊቲ .....በቅሊንጦ.....በዝዋይ...በሸዋ ሮቢት.....በድሬዳዋ እስር ቤቶች ከ35 ሺህ በላይ እስረኞች የሚገኙ ሲሆን እስር ቤቶቹ በቆርቆሮ የተሰሩ በመሆኑ ብዙዎቹ በብርድ በሽታ እየሞቱ እንደሆነም ይሄው የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

በተለይ በአዲስ አበባ በቃሊቲ እስር ቤት በአንድ ዞን ብቻ 4 ሺህ እስረኛ በመታጎሩ እስረኞች ለአስምና ለሌሎች በሽታዎች ተዳርገው እየተሰቃዩ ከመሆኑም በላይ በቂ ህክምናም እንደማያገኙ የእስረኛ ቤተሰቦች ተናግረዋል፡፡